ዱንያ ለአማኞች እስር ቤት ለከሃዲዎች ጀነት ናት።

ከአቡ ሁረይራ - አላህ መልካም ሥራቸውን ይውደድላቸውና - እንደተላለፈው እንዲህ አሉ፦ «የአላህ መልክተኛ -የአላህ ሰላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - እንዲህ ብለዋል፦ "ዱንያ ለአማኞች እስር ቤት ለከሃዲዎች ጀነት ናት።"» [ሶሒሕ ነው።] [ሙስሊም ዘግበውታል።]

ነቢዩ - የአላህ ሶላትና ሰላም በእርሳቸው ላይ ይስፈንና - አማኝ የሆነ ሰው በዱንያ ትእዛዛትን በመፈፀምና ክልከላን በመራቅ በኩል ሸሪዓዊ በሆኑ ሃላፊነቶች ስለታሰረ የዱንያ ህይወት ለአማኝ እስር ቤት እንደሆነች እና ከዚህም ሲሞት አላህ ለርሱ ወዳዘጋጀለት ዘውታሪ ፀጋ ተሸጋግሮ እንደሚያርፍ ተናገሩ። ከሃዲ የሆነ ሰው ደግሞ ነፍሱ የፈለገችውን ሁሉና ዝንባሌው የመራውን ሁሉ ስለሚሰራ ዱንያ ለከሃዲ ጀነት መሆኗንና ሲሞትም አላህ የትንሳኤ ቀን ወዳዘጋጀለት ዘውታሪ ቅጣት ይሸጋገራል ብለው ተናገሩ።

http://sunnah.global/hadeeth/am/show/3584